1. ተናገሩ

ተናገሩ ድንቅ ሥራውንም መስክሩ/2/
ተአምሩን ለዓለም ንገሩ/2/
ድንቅ ሥራውን መስክሩ } 2

2. ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር/2/ **ምስጋና ይገባሃል**/2/
ለዚች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም
በጤና አደረስከን

3. እስመ አልብነ ረዳኢ

እስመ አልብነ ረዳኢ በጊዜ ምንዳቤ ወኃዘን/2/
እስመ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር/4/

<u>ትርጉም</u>፣ በችግርና በሐዘን ጊዜ የሚረዳን የለም እኛ ከአንተ በቀር ሌላ አናውቅምና

4. በወጀብ

በወጀብ በዐውሎ ውስጥ በመከራዬ ቀን/2/
ረድቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን
አድኖኛልና እግዚአብሔር ይመስገን

5. ኵሉ ዘፈቀደ

ኵሉ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር/2/ } 2
በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኵሉ ቀላያት/4/

<u>ትርጉም</u>:–*እግዚአብሔር በሰማይና በምድር በባሕርም በፈሳሾችም ሁሉ የወደደውን አደረገ*

6. ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው/2/
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/
በትጋት ተራምደን እንግባ በጠዋት/2/
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት/2/
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/
ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

7. ኖላዊ ትጉህ

ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም/2/
ማኅበረነ/2/ **ዕቀብ በሠላም**/4/
የማታንቀላፋ ተጉህ እረኝችን/2/
ጠብቅልን በሰላም ማኅበራችንን/2/

8. ነአምን በአብ

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ በወልድ/2/
ወነአምን/4/ **ነአምን በመንፈስ ቅዱስ**/2/
እናምናለን በአብ እንምናለን በወልድ/2/ /2
እናምናለን/5/ **በመንፈስቅዱስ**/2/

9.እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው/2/ } 2
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው/2/
አምላኬ መመኪያዬ ነው

10.. መድኃኔዓለም አዳነን

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ/2/
<u>ደስ ይበለን</u>/2/ **<u>እልል በሉ</u>**/2/**አዳነን**
በማይሻር ቃሉ

11. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነተህ
አመሰግንሃለሁ እልል/2/ } 2
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም/2/

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አዝ
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ

ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
አዝ
ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ
በቀንም በሌሊትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ ዕጹብ ለአንተ ሥራ
አዝ
አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

12. አማን በአማን

አማን በአማን/4/
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም/4/

<u>ትርጉም</u>፣ እውነት በእውነት
የሥላሴ መንግሥት ዘለዓለማዊ ነው።

13. የኃያላን ኃያል

የኃያላን ኃያል/3/ ልዑል እግዚአብሔር/2/
ተአምራትህ ብዙ በሰማይ/2/ በምድር } 2
ተአምራትህ ብዙ በሰማይ/3/ በምድር }

14. ፍቅር ሰሐቦ

ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እምመንበሩ/2/
ወአብጽሐ/3/ እስከለሞት/2/
<u>ትርጉም</u>፣ፍቅር ኃያል ወልድን ከልዑል መንበሩ
ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው።

15. ንሴብሖ

ንሴብሖ/2/ ለእግዚአብሔር/2/
ስቡሓ ዘተሰብሓ/4/
እናመስግነው /2/ እግዚአብሔርን/2/
ምስጉን ነው የተመሰገነ/4/

16. ጸጋ ነሳዕነ

ጸጋ ነሳዕነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ } 2
መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ በኃይለ }
መስቀሉ

ኪያከ እግዚኦ ነአኩት ወንሴብሓከ
እግዚአብሔር/2/

17. በክንፈ ረድኤትህ

እንደ ዓይን ብሌን አምላክ ሆይ ጠብቀኝ/2/
በክንፈ ረድኤትህ ከመዓትም ጋርደኝ/4/

18. ኃይል የእግዚአብሔር ነው

ኃይል የእግዚአብሔር ነው
ማዳን የእግዚአብሔር ጥበብ
የእግዚአብሔር
አንመካም በጉልበታችን
እግዚአብሔር ነው የኛ ኃይላችን

19. ዘሰማየ ገብረ

ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድረ
ሣረረ/2/
አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ/4/
ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና/2/
ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለ እርሱ ማን
አለና/2/

20. ንሰሐ እንግባ

ንሰሐ እንግባ ኃጢአት መሥራት ይቅር/2/
የአምላክ ባለሟሎች እንሁን በምግባር } 2
የአምላክ ባለሟሎች እንሁን }

21. ሰላምህን ስጣት

ሃሌ ሃሌ ሃሌሉያ/2/
ሀባ ሰላምከ ለኢትዮጵያ/4/
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/
ሰላምህን ስጣት ለኢትዮጵያ/4/

22. ንሴብሖ

ንሴብሖ/2/ ለአምላከ ዕዝራ/2/
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጠ ስለፍቅርህ ልጆምር ማኅሌት

ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

አዝ

ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሃን
አስገረመኝ ከዋክብቱ ሲያወሩ ሥራህን
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

አዝ

አእዋፉ በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በምሥጢር ሲያወሩ
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

አዝ

ከበሮ ሆይ ጸናጽል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

አዝ

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ስለሁሉም ነገር
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ

አዝ

23. ኢትዮጲያ ታበጽህ እደዊሃ

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ኃበ እግዚአብሔር/2/ } 2

እንዘትብል አምላኪዬ/2/ ነጽረኒ ወአድኅነኒ
እምኃይለ ጸላኢ ወፀር } 2

ትርጉም፣ በምሕረት ዓይን ተመልከተን ከጠላት ኃይል አድነን እያለች ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች

24. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን
እከፍለዋለሁ/2/
ተመስገን ነው እንጂ/2/ ሌላ ምን
እላለሁ/4/

25. እናመሰግን አማኑኤልን

እናመሰግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ/2/
በሞቱ ሞትን ሻረልን እንዳንረታ/4/

26. የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት } 2
አእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እደት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት /2/

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ልዩ ክብር ሊያዩ የታደሉ
በጽድቅ ሥራቸው ደምቀው ይታያሉ /2/

አዝ . . .

የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር
ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ /3/

አዝ . . .

27. ለአምላካችን እንዘምር */ብዙአየሁ ተመስገን - ቁ.1/*

ለአምላካችን አንዘምር ለጌታችን እንዘምር /2/
ብዙነው ውለታው የእግዚአብሔር /2/ } 2

ወደእኛ ለመጣው ከሰማያት ወርዶ
በበረት ለተኛው ከድንግል ተወልዶ
ለሰው ልጆች ፍቅር ሰው ለሆነው ወዶ/2/

አዝ ....

እኛ ለተሰደድን ለተሰደደልን
ተጠምቆና አጥምቆ አርአያ ለሆነን
በበደልነው ሁሉ እርሱ ለካሰልን/2/

አዝ ....

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለፀው
ዓለምን ለማዳን ደሙን ላፈሰሰው
ለቸሩ ክርስቶስ ምስጋና ይድረሰው /2

አዝ ....

ለሐዘን ለደስታ ስለደረሰልን
በኑሮአችን ሁሉ ስለቀደመልን

በበጎ ስጦታው ፍቅሩን ላበዛልን /2/
አዝ ....
ስለቸርነቱ ብዙ አድርጎልናል
ታዲያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈለዋል
ሰዎች ዝም አንበል ማመስገን ይገባል
አዝ ....

.28. እናመሰግነው

/ተስፋዬ ኢዶ - ቁ.2/

እናመሰግነው /2/
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው /2/

ከኃጢአት ቀንበር ከሞት ቤት ለይቶ
መንግሥቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘለዓለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለኝ
መቼም የማይተወኝ ታላቅ አባት አለኝ
አዝ ....
ፍጡራን ቢንቁኝ መጎሰቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋቢስ ነህ ብለው
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መች ተወኝ
ሁለት እጁን ይዞ ልጁ ተነስ አለኝ
አዝ ....
ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ላደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን
ለታላቅ ውለታው ጌታ ለዋለልን
በእልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን
አዝ ....

29. የቀደመ በደላችንን /አዳነች አስፋው - ቁ. 2/

የቀደመ በደላችንን /2/
<u>አታስብብን</u> /2/አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ
ይደረግልን /2/አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ
ይሁን ይደረግልን /2/

30. ተነሱ እንዘምር

ተነሱ እንዘምር /2/
በአንድነት ሆነን በእልልታ /2/ □ሽ
/3/ ምስጋና በሰማይ ምስጋና
በምድር /2/ለኃያሉ ጌታ ለልዑል
እግዚአብሔር

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል
አዝ . . .
አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው
አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት የአንተ ሥራ የአንተ ልዕልና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና
አዝ . . .
ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ
በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ
ከእንቅፋት ከድንጋይ ትሰውረናለህ
አዝ . . .
ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታህ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከማታ
ሌላ ምንም የለን የምንከፍልህ ጌታ
አዝ . . .
መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን እናውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከዘለዓለም ለስምህ እንዘምር
አዝ . . .

31. ኖላዊ ትጉህ

ኖላዊ ትጉህ /2/
ሐውጸነ /2/ በምሕረት ብዙኅ። □ኽ
/4/
<u>ትርጉም፦</u> ቸር ትጉህ ጠባቂ ሆይ በብዙ ምሕረት ቸርነት ጎበኘን።

32. አምላካችን ተመስገን

አምላካችን ተመስገን/2/ ለዛሬ ያደረስከን
አምላካችን ተመስገን /2/ ለዚህ ቀን
ያደረስከን

በኃጢአት ስንማቅቅ በምሕረትህ ጠራኸን
በዓለም ስንባዝን ነበር በይቅርታህ መራኸን

አምላክ ሆይ ተመስገን
ትእግስትህ ብዙ ነው አያልቅም ርኅራሄህ
የምከፍልህ ምን ይሆን ብዙ ነው ውለታህ
አምላክ ሆይ ተመስገን

አዝ
ከቶ የማትፈልግ ከሰው ልጆች ወረታ
ቸር ፈጣሪ ነህና ሥራህ ድንቅ ነው ጌታ
አምላክ ሆይ ተመስገን
ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ አንተን
እናመልካለን
ከመዓትህ ታግሰህ ሁሉንም ይቅር አልከን
አምላክ ሆይ ተመስገን

አዝ
ኃጢአታችን ጨለማ ቢያደርገው
ኑሮአችንን
በአንተ ተጐናጽፈናል የማዳንን ብርሃን
አምላክ ሆይ ተመስገን
ስለአደረክልን ሁሉ ስለ ግሩም ሥራህ
የራስህን እንስጥህ ተመስገን እንበልህ

አዝ

33. ያከበርዋ ለሰንበት

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት
ጻድቃን በውስተ ገነት
ወኩሉ ፍጥረት ዓሣት ወአናብርት
እለ ውስተ ደይን ያዕረፉ ባቲ
እስመባቲ አዕረፈ እምኩሉ ግብሩ
ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት
ጻድቃንም በገነት
ፍጥረታት በሙሉ ዓሣዎችና አንበሪዎች
በመቃብር ያሉ ያከብሯታል
አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ

34. እልል ደስ ይበለን

እልል እልል ደስ ይበለን ልመናችንን አምላክ
ሰማን /፪/
እናመስግነው/4/ ይገባዋል ሁሉን ፈፃሚ
ነው<u>እሺ</u>/3/

35 ንሴብሆ

ንሴብሆ/፪/ ለእግዚአብሔር /፪/
ስቡህ ዘተሰብህ/፬/
እናመስግነው/፪/ እግዚአብሔርን/፪/
ምስጉን ነው የተመሠገነ/፬/

36 አምላካችን ጸመልን

አምላካችን ጸመልን አርባውን ቀን/፪/
ምሣሌውን ሊሠጠን ምሣሌውን/፬/

37 ንጉሥ ውእቱ

ንጉሥ ውእቱ ንጉሠ ሠላም/፬/
አምላክነ/፪/ መድኃኔዓለም/፬/

38 ንግሥት ይእቲ

ንግሥት ይእቲ ንግሥተ ሰላም/፬/
ማርያም/፪/ ኪዳነ ምህረት /፬/

39 ***ሠራዊተ መላእክቲሁ***

ሠራዊተ መላእክቲሁ /፪/
ለምድኃኔዓለም/፪/ ይቀውሙ·/፬/

ትርጉም፡-

40..ዘይክል ኩሉ

ዘይክል ኩሉ አልቦ ዘይስዓኖ ለእግዚአብሔር
አምላክ ነዳያን ረዳኤ ምነዱባን
ንህነ ሀቤከ /2/ ተማህፀነ
የድሆች አለኝታ ተስፋ ላጡ ተስፋ
ሁሉንም የምትችል ደራሽ ለተከፋ
ለኛም ድረስልን በኃጢአት ሳንጠፋ
አዝ--- ናዛዜ ህዙናን
ከገነት ሲባረር አዳም ተሳስቶ
ባለቀሰ ጊዜ ልጅነቱን አጥቶ
ትድናለህ ብለህ ያዳንከው በመስቀል
የቅዱሳን አምላክ አቤቱ ቸል አትበል
አዝ --- ወተስፋ ቅቡዓን

ህዝበ እስራኤልን ፈርያን ሲገዛቸው
ጭንቅና መከራ እያፀናባቸው
በእነራሔል ለቅሶ ሙሴን ላክላቸው
አዝ --- ረዳኤ ምንዱባን
እኛ ወገኖችህ ወደ አንተ እንጮህለን
ከጭንቅ ከመከራ እንድትታደገን
ጌታ አንተ ነህና ናዛዜ ህዙናን
ዘይክል ኩሉ አልቦ ዘይስዓኖ ለእግዚአብሔር
አምላከ ነዳያን ናዛዜ ህዙናን
ንህነ ኃጌከ /፪/ ተማህፀነ
ዘይክል ኩሉ አልቦ ዘይስዓኖ ለእግዚአብሔር
አምላከ ነዳያን ወተስፋ ቅቡፃን ንህነ ኃጌከ
/፪/ ተማህፀነ

41. የድንግል ልዕልና
አሁን ተገለጠ የድንግል ልዕልና } 2
ከእርሷ ተወለደ ሰማያዊ መና
አምላከ አማልክት ቀዳማዊ ቃል } 5
በአንቺ ላይ አደረ ማርያም ድንግል
ከሰማይ ወደ ምድር አብ ቢመለከት } 2
ምንምአላገኘም እንደ አንቺ ንጽሕት
መላእክት በሰማይ እጎታችን ይሉሻል
በንጽሕ በድንጋሌ እነርሱን መስለሻል } 2

42. በኮከብ መፅሉ
በኮከብ መፅዉ መፅዉ ሰብአ ሰገል/2/
ለአማኑኤል/4/ ይስግዱ ለአማኑኤል/2/
<u>ትርጉም</u>፦የጥበብ ሰዎች በኮከብ እየተመሩ
መጡ ለአማኑኤል ይሰግዱ ዘንድ

43. ሣር ቅጠሉ ሠርዶው
ሣር ቅጠሉ ሠርዶው ሠንበሌጥ ቄጠማው
በዚያች ወር በዚያች ቀን ለምለም የነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው
ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው
እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ
የፍቅር የሰላም ንሸና ገበያ/2/
የታደሉ እረኞች ያደሩ በትጋት
ብርሃን ሆነላቸው በዕኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ ሠራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
አዝ፣
እረኝነት ትንሽ የወራዳ ግብር
ብሎ ሰው በልማድ ደንግጎ ነበር
አምላክ የመረጠው መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ
አዝ፣
የተነበዩለት ነቢያት በሙሉ
ጌታ ተወለደ የምሥራች በሉ
ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉሥ } 2
ይኸው ተወለደ እኛን ለመቀደስ
አዝ፣
የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ሰብአ ሰገል } 2
ሰምተው
ሊሰግዱለት መጡ በኮከብ ተመርተው } 2
ዕጣንና ከርቤ ወርቁንም አመጡ
እንደየሥርዓቱ እጅ መንሻን ሰጡ } 2
አዝ፣
ስለተወለደ መድኅን የኛ ተስፋ
በደል ተወገደ ኃጢአትም ጠፋ } 2
አዝ፣

44. ስብሐት ለእግዚአብሔር
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት/2/
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሃሌ
ሉያ
ሃሌ ሉያ /3/ ሃሌ ሃሌ ሉያ
<u>ትርጉም</u>፦ ለእግዚአብሔር በሰማያት
ምስጋና ይገባዋል በምድር እርቅ ተጀመረ
ለሰው ግዕዛኑ/ንፃንቱ/ ሊሰጠው

45. በጐል ሰከበ
በጐል ሰከበ በአፅርቅት ተጠብለለ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም/2/ ዮም ተወልደ/4/
በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ/2/
የዓለም መድኃኒት/2/ ዛሬ ተወለደ/4/

46. የጥበብ ሰዎች መጡ

ሰማይና ምድር የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ
የጥበብ ሰዎች መጡ/2/ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደ ፋና/2/
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
ካንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርስን
አዝ...
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት
አዝ...
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእሥራኤል ንጉሥ ወዴት አለ እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ
ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ
ከርቤውን ለሞቱ
አዝ...

47. ይኸው ተወለደ

ይኸው ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/
እሰይ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/
ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ በሙሉ
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ
አዝ፣
ሰብአሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእስራኤል ንጉሥ ተዋልዷል እያሉ
አዝ፣
ሰብአሰገል መጡ እጅ መንሻ ይዘው
ወርቅ እጣን ከርቤውን ገበሩለት ሰግደው
አዝ፣
ሕፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት
ውኃ ሆኗልና ማርና ወተት
አዝ፣

48. ለዘተወልደ እምቅድስት

ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል
ምንተንብሉ
ናስተማስሎ ለመድኃኒነ
አርዌ ገዳምኑ አንበሳ ወሚመ/2/ ከራድዮን
<u>ትርጉም</u>፣ከእመቤታችን የተወለደውን ምን
ብለን እንጠራዋለን። መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስን በምን እንመስለዋለን በዱር
አንበሳ ነው ወይስ ከራድዮን በሚባል ወፍ ነው።

በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ

49. ሖረ ኢየሱስ

ሖረ ኢየሱስ/4/
እምገሊላ/2/ ኀበ ዮርዳኖስ
ፈለገዮርዳኖስ/2/ ከመያጥምቆ
<u>ትርጉም</u>፣ ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ
ወረደ በዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠመቅ

50. ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /6/
እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት/2/
<u>ትርጉም</u>፣ ወልድ ክርስቶስ ከሰማያት
ወደ ወንዞች ወረደ

51. ውስተ ማኅጸነ ድንግል

2 ውስተ ማኅጸነ ድንግል ኀደረማኅፀነ ድንግል
ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ
ሰማይ ወምድር በማይ ተጠመቀ
<u>ትርጉም</u>፣ ሰማይና ምድር የማይችሉት አምላክ
በእመቤታችን ማኅጸን አደረ በውሃ ተጠመቀ

52. መጽዐ ቃል

መጽዐ ቃል እም ደመና ዘይብል/2/
ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር/4/
መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል/2/
የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው/4/

53. የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ
አዝ
ባሕር ተጨነቅች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ
አዝ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት
አዝ
እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ
አዝ
ባሕር ስትጨነቅ ተራራ ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመና ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምሥጢር
አዝ

54. አማን በአማን

አማን በአማን አማን በአማን/2/
መንክር ስብሐተ ጥምቀቱ/4/
እውነት ነው በእውነት /4/
ድንቅ ነው የጌታ ጥምቀት/4/

55. በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/
ሰማያዊ/5/ ኢየሱስ ናዝራዊ /2/

<u>ትርጉም፦</u> ሰማያዊው የናዝሬቱ ኢየሱስ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

56. ተጠምቀ ሰማያዊ

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/
ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ መፈታዊ/4/
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ } 2

57.ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር/፪/
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም /፬/
እናመሰግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/፪/
የዓለም ቤዛ ነውና የማህፀንሽ ፍሬ/፬/
ከሠማይ ሠማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ/፪/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ/፬/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ዕዳችንን ፋቀ/፪/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን/፬/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺን ፅንስ/፪/
የድኩማኖች ብርታት ነው የህሙማን ፈውስ/፬/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ/፪/
በመንግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ/፬/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ/፪/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ/፬/
እመቤታችን እናታችን ማርያም/፪/
የተማፀነሽ ይኖራል ለዘለዓለም/፬/

በእንተ በዓለ ሆሣዕና

58.. ሆሣዕና እምርት

ሆሣዕና እምርት እንተ አቡነ ዳዊት/2/

ቡርክት እንተ ትመፅዕ መንግሥት/4/

<u>ትርጉም፦</u> የታወቀች የድኅነት ቀን
የምትመጣይቱ የአባታችን የዳዊት
መንግሥት ቡርክት ናት

59.. ሰላምሽ ዛሬ ነው

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም

ወደ አንቺ መጥቷልና አምላክ ዘለዓለም/2/

ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕፃናት በኢየሩሳሌም

አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ

የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ/2/

አዝ

ሆሣዕና እያሉ አመሰገኑት

በኢየሩሳሌም አእሩግ ወሕፃናት/2/

አዝ

ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙት

መስቀል ተሸክሞ ሆነን መድኃኒት/2/

አዝ

የኢየሱስን ሕማም ደናግል አይተው

እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው/2/

60. እም አፈ ደቂቅ

እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ

ስብሐት/2/

በእንተ ፀላዒ/4/ ከመትንሥዖ ለፀላዒ

ወለገፋኢ /2/

<u>ትርጉም፦</u>ከሕፃናት እንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ የጠላት
ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስ ዘንድ

61. ሆሣዕና በአርያም

ሆሣዕና/2/ በአርያም ሆሣዕና በአርያም

ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም

ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም

አዝ

በአህያ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ የገባው

ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነዉ

አዝ

ኃይልና ስልጣን በአንድ ላይ ስላለው

ጠላቶችሽ ፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው

አዝ

62. የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ/2/

ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/2/

የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት/2/

በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/2/

ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አሥሮ/2/

ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተባብሮ/2/

ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ/2/

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2/

በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ/2/

በችንካር ላይ ሆነው ምንም አልሰለቹ /2/

የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ/2/

የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ/2/

63. ስለኛ ብሎ

ስለኛ ብሎ ልጅሽ ተሰቅሎ

ልብሽ በኀዘን ተወግቶ ቆስሎ/2/

ከመስቀሉ አውርደውት

ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ደግፈውት

ያለቀሰሽው የዕንባሽ ብዛት

ይጠብልን የእኛን ኃጢአት

64. ሙታንን ያድን ዘንድ

ሙታንን ያድን ዘንድ የሞትሞትን ሽሮ/2/
ወልደ አምላክ ሄደ ወደ ኋላ ታሥሮ/2/

ግርማን ለኪሩቤል ያጐናጸፋቸው

ዘውድን ለሱራፌል የሚያቀዳጃቸው

ከለሜዳ ለብሶ ዋለ ከፊታቸው

አዝ

ቅዱሳን እጆቹ አዳምን የሠሩት

ቅዱሳን እግሮቹ በገነት የዞሩት

ተቸንክረው ዋሉ በጠንካራ ብረት

አዝ

ምን በበደለ ነው ምን ባደረገ ነው /2/

ወልድ እንደ ቀማኛ ሲገረፍ የዋለው

አዝ

አዳም በበደለ የግፍ ግፍ በሠራ

ቸሩ ወልደ አምላክ ዋለ በመከራ

አዝ

ሁሉንም ታገሰ ሁሉን ቻለ ሆድህ

ትልቁም ትንሹም ሲዘባበትብህ

65 ሰቀሉ ምሰሌሁ

ሰቀሉ ምስሌሁ ክልኤተ ፈያተ/2/በየማኑ ወበፀጋሙ/2/

ወበማዕከሌሙ/2/ ኢየሱስ/2/ ወበማዕከሌሙ ኢየሱስ/2/

<u>ትርጉም፣</u> ከርሱ ጋራ አንዱን በቀኙ አንዱን በግራው አድርገው ሁለት ሽፍቶችን ሰቀሉ። ኢየሱስንም በመሐል

66. በጌቴ ሴማኒ

በጌቴ ሴማኒ በአትክልቱ ቦታ/2/

ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/

አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት/2/

ለእኛም ነበረብን የዘለዓለም ሞት/2/

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ/2/

ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ/2/

ድንግል አልቻለችም ዕንባዋን ልትገታ/2/

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2/

በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /2/

እንዲህ ሲል ጸለየ አባት ማራቸው/2/

በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ/2/

በሰዎች ተገርፎ ሞቶ ተቀበረ/2/

ፍቅሩን የገለጸው ተወልዶ በሥጋ/2/

ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና ዖሜጋ/2/

67. ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አማጽያን ሰቀሉህ ወይ

የዓለም መድኃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ ወይ/2/

የአዳም በደል አደረሰህ አንተን ለመሰቀል

የሔዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ አባት/2/

ንጹሕ ክርስቶስ ሆንክ ወንጀለኛ ብለህ ስለኛ

መስቀል አሸክመው አሥረው ገረፉህ እያዳፉህ/2/

እጅና እግርህ በብረት ተመታ የዓለም ጌታ

የእሾህ አክሊል ደፍተህ ጐንህም ተወጋ አልፋ ዖሜጋ/2/

ግብዞች እንደራሳቸው መስሎአቸው

ምራቅ እየተፉ በፊትህ ቀለዱ አንተን ሊጐዱ/2/

በመስቀል ላይ ተጠማሁ ስትል ታላቅ በደል

ሐሞትና ከርቤ ሰጡህ ቀላቅለው ጠጣ ብለው/2/

ይቅር ባይ በደላችንን ሁሉን ስታይ

አንተ ይቅር በለን በእኛ ሳትከፋ እንዳንጠፋ/2/

68. መስክሪ ቀራንዮ

መስክሪ ቀራንዮ ንገሪን ጐልጐታ

ካሣ እንደሆነልን እንደ አዳነን ጌታ

በአምላክነቱ ፈጥሮ ዓለማችን

ሥጋን መዋሐዱን ሰዎችን ለማዳን

ክብሩን ዝቅ አድርጎ በታላቅ ትኅትና

ሞትን ሊያጠፋልን ያየውን ፈተና

አዝ

ለፍርድ ሲወስዱት ሊቀበል መከራ

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ

አይሁድ በየተራ ሲገርፉት ሲያዳፉት

እንደታገሳቸው በፍፁም ቸርነት

አዝ

ምንም ሳያጠፋ በደል ሳይኖርበት

በመስቀል እንዲሞት ቅጣት ተፈርዶበት

ወደ ኋላ ታሥሮ ተገርፎ ተመትቶ
ያየውን መከራ የሾህ አክሊል ደፍቶ
አዝ
በሞቱ ሙታንን ከመቃብር ጠርቶ
በእርሱ ውርደት ክብርን ለሰው ልጆች
ሰጥቶ
በሕይወት እንድንኖር ዳግም እንዳንሞት
ትንሣኤን መስበኩን በከበረች ሰንበት
አዝ

69. ዘአልበስዎ

ዘአልበስዎ አይሁድ ከለሜዳ ዘለይ/2/
እኽ ከለሜዳ ዘለይ/2/ ከለሜዳ/2/
<u>ትርጉም</u>፣ አይሁድ ጌታችንን ቀይ
ግምጃ አለበሱት

70. እስመ ለዓለም ምሕረቱ

እስመ ለዓለም ምሕረቱ/2
ኢያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት
መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት
አዝ
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው/2
ከገሃነም እሳት እኛን ሊያድን ነው/2
አዝ
ከማርያም የነሣው ያ ቅዱስ ሥጋው
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው
አዝ
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ለይቶ/2
አዝ

በእንተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ

71.ትንሣኤከ

ትንሣኤከ ለእለ አመነ/2/
ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ/4/
ትንሣኤህን ለምናምን ለእኛ/2/
ብርሃንህን ላክልን ወደእኛ/4/

72. አማን በአማን

አማን በአማን/4/
ተንሥአ እምነ ሙታን /2/
እውነት በእውነት /4/
ተነሣ ዛሬ ከሙታን /2/

73. እም እቶነ እሳት

እም እቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ/2/
ብርሃናተ ዘይትአጸፍ ተንሥአ ለነ/4/
ከሚነደው እሳት ከነበልባሉ አወጣን/2/
ብርሃናትን ተጎናጽፎ ተነሣልን/4/

74. ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ

ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ /2/
ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ/4/
ምድር ጸዳች ሐሴት አረገች/2/
በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች/4/

በእንተ ዕርገቱ ለእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ

75. ዐረገ በስብሐት

ዐረገ በስብሐት ዐረገ በዕልልታ
በስብሐት በዕልልታ ዐረገ/2/ በዕልልታ/2/
ሞትን ድል አድርጐ የሠራዊት ጌታ
ዐረገ/2/ በዕልልታ

መዝሙረ ጸራቅሊጦስ

76.አንትሙሰ ንበሩ

አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም/2/
እስክትለብሱ ኃይል እም አርያም/4/
እናንተ ግን ቆዩ በኢየሩሳሌም ሀገር/2/
እስከምታገኙ ኃይል ከሰማይ/4/

77. መንፈስ ቅዱስ ወረደ

መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት/2/
ተመሲሎ /5/ በነደ እሳት/2/

<u>ትርጉም፣</u> መንፈስ ቅዱስ በእሳት
አምሳያ በሐዋርያት ላይ ወረደ

በእንተ ምፅአቱ ለእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ

78. አምላክ ሆይ ማረን

እውነተኛው ንጉሥ ለፍርድ ሲመጣ
ጻድቁን ሊያከብር ኃጥኡን ሊቀጣ
መለከት ሲነፋ ነጐድጓድ ሲሰማ
ክርስቶስ ሲገለጥ በሚያስደንቅ ግርማ
አምላክ ሆይ ማረን
ማረን አምላክ ይቅር በለን } 2
የነበረው ሁሉ ሲሆን እንዳልነበር
ተነሥተው ሲቆሙ ሙታን ከመቃብር
ፀሐይ ስትጨልም ሰማያትም ሲያልፉ
ምድር ቀውጢ ስትሆን ቀላያት ሲጠፉ
አዝ
ፍጥረት ሲናድ ሲርድ ግርማው እያስፈራው
የአዳም ዘር በሙሉ ሲቆም ከነሥራው
ማነው የሚገኘው በጌ ምግባር ሠርቶ
ቅዱሳንን መስሎ በሃይማኖት ጸንቶ
አዝ
በምድራዊ ሕይወት ትሩፋት የሠሩ
ጻድቃን ሲደሰቱ ተግተው ሲዘምሩ
ኃጥአን ሲጠፉቸው የሚሰወሩበት
እኛስ ከየት ይሆን የምንገኝበት
አዝ

79. አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ

አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ ለብሰህ
የማርያምን ሥጋ /2/
ባክኖ የነበረው የአዳም ልጅ ውጤቱ ነበር
የሚያሰጋ/2/
በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን
ድኅነትን
ለሰው ልጅ ስትሰጥ/2/
ምን የበዛ ነበር ትኅትናህ ትዕግሥትህ
የማይለወጥ/2/
የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጐንህን
ሲወጉህ በጦር/2/
አንተ ግን ለእነርሱ ከአባትህ ምሕረትን
ትለምን ነበር/2/
ግን መቼ አወቁህ እነርሱ በኃጢአት
ደንድኖ ልባቸው/2/
መድኃኒታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም
ሞትክላቸው /2/
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍፃሜ
በኋላ/2/
ኧረ እንዴት እድለኞች ናቸው በፊትህ
የሚያገኙ ተድላ/2/
በዚያች በደብረዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ
ሲፈልቅ/2/
ከቶ ወዴት ይሆን እጣዬ ያንጊዜ የእኔ
አወዳደቅ/2/
የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ
እኔን/2/
እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው
ልቤን/2/

80 ፀንተን እንጠብቅ

ከመላእክት ጋር ሲገለጥ በሰማይ
ፀንተን እንጠብቀው ክብሩን ሁሉ እንድናይ
በግርማ ሲመጣ በአስደንጋጭ ሁኔታ
ወዮልሽ ነፍሴ ሆይ ወየው የዛን ለታ
ኧኸ ምሥጋና ይድረስህ ሁልጊዜ ጠዋት ማታ
ሃሌ ሃሌሉያ የሠራዊት ጌታ/2/
ሰማይና ምድር ከፊቱ ሲሸሹ
መግቢያ አጥቶ ይጮሃል ትልቁም ትንሹ
ጻድቃን ሲደሰቱ የኃጥአን ፋንታ
ሆኖ ጠበቃቸው ለቅሶና ዋይታ
አዝ
ስለማይታወቅ አምላክ አመጣጥህ

በሃይማኖት አፅናን ተግተን እንጠብቅህ
ጠላት እንዳይገዛን በእርሱ እንዳንረታ
እግዚአብሔር አድነን ሁንልን መከታ
አዝ

81. አንድ ቀን አለ
አንድ ቀን አለ የሚያስፈራ
ለጻድቃን የሚያበራ/2/
ጌታ በዚያች ቀን ይመጣል
በግርማ ይገለጣል /2/
የፍርድ አዋጅ ይታወጃል
ነፍስ ሁሉ ይጨነቃል
ኃጥአን ያለቅሳሉ
በግራህ ይቆማሉ/2/
ቅዱስ ቃሉን ሰምተው ያመኑ
የፀኑ በኪዳኑ /2/
ተከብረው በቀኙ ይቆማሉ
ከኃዘን ይሰወራሉ
መሐሪ ጌታ ፈጣሪያችን
ይድረስህ ልመናችን /2/
በዚያች ግሩም ቀን እባክህ
አቁመን በቀኝህ/2/

መዝሙር ዘዘወትር -
ዘድንግል ማርያም
82. ፀሐይኑ ንብለክ
ፀሐይኑ ንብለክ/2/ ወልደ ማርያም ንብለክ/2/
በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለክ/4/
ፀሐይኑ ንብለኪ /2/ ወላዲተ ቃል ንብለኪ
በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ/4/

83. እንበለ ምግባር
እንበለ ምግባር ባሕቱ እመ ኢይፀድቅ አነ/2/
ቦኑ ለከንቱ ኪዳንኪ ኮነ ቦኑ ለከንቱ
ኪዳንኪ ኮነ/2/

<u>ትርጉም</u>፣ ምንም እንኳ ሥራዬ ለዚያ የሚያበቃ ባይሆን መንግሥተ ሰማያትን የምወርሳት ካልሆነ እመቤቴ ሆይ ቃል ኪዳንሽ ለከንቱ ነውን።

84. ለምኝልን ማርያም
ለምኝልን/2/ ማርያም ለምኝልን/2/
የንፁሐን አክሊል/2/ የቅዱሳን ብርሃን/2/

85. ኑይ ኑይ
ኑይ ኑይ ማርያም ወላዲተ አምላክ
የፃድቃን እመቤት የመላእክት እኅት } 2
ሁላችሁ እመኗት ከልብ አማላጅ ናትና
በእውነት እናመስግናት እናወድሳት } 2
አማላጅ ኪዳነ ምሕረት

86. እንተ በምድር
እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ
አዕዉቂሃ/2/
ሐረገ ወይን/2/ ድንግል ሐረገ ወይን/2/
<u>ትርጉም</u>፦እመቤታችን ሥሯ በምድር
ቅርንጫፏ በሰማይ የሆነ የወይን ሐረግ ናት

87. በምድራዊ ሕይወት
በምድራዊ ሕይወት/2/ በፈተና ቦታ/2/
ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ
ድንግል ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ/2/ } 2

88. ኪዳነ ምሕረት
ኪዳነ ምሕረት እመቤት } 2
ለዓለም ሁሉ መድኃኒት
ቅድስተ ቅዱሳን ብፅዕት
አንቺ ነሽ ለአምላካችን እናት
ጌታችን ፈጠረሽ ልዩ አድርጐ
በሚያስደንቅ ምሥጢሩ ለተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያለ ሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና
አስተባብረሽ ይዘሻልና
ድንግልም እናትም እመብርሃን }

ንጽሕተ ንጹሐን እኖን አማልጅን 2

89. ሰላም ለኪ ማርያም

ሰላም ለኪ ማርያም እመ አምላክ/2/
ወልድኪ ይጼውአኪ ውስተ ሕይወት } 2
ወመንግሥተ ክብር

ትርጉም፣ የአምላክ እናት ማርያም ሰላም እልሻለሁ ወደ ሕይወትና ክብር ወዳለው ጌትነት ልጅሽ ይጠራሻል

90. በዝናመ ንጽሕኪ

በዝናመ ንጽሕኪ ሐረገ ወይን ጸገየ/2/
ወሮማን ወሮማን/2/ ወሮማን ሐዋዘ ፈረየ

ለአዳም ተስፋ የሆንሽው ማርያም እመቤቴ/2/
አማልጂኝ ቶሎ ብለሽ/3/ ሳልጠፋብሽ ልጅሽ
የዳዊት መሰንቆ ነሽ የኢያሱም ሐውልት/2/
በምን ልመስልሽ/3/ ወደርም የለሽ
እመቤቴ ጥላዬ ሁኝልኝ ከለላዬ/2/
ያለ አንቺ ማን አለኝ/3/ አለሁሽ/ህ/ በይኝ

አዝ

በአንዱ በልጅሽ ተማጽኜሻለሁ
በቃል ኪዳንሽ ተማጽኜሻለሁ
ድንግል ሆይ ጠብቂኝ ክፉ እንዳልናገር
ከምስጋናሽ ከበጐ በስተቀር

አዝ

በአምስቱ ኃዘኖችሽ ተማፅኜሻለሁ
በረሃብ በጥምሽ ተማፅኜሻለሁ
በኃዘን በስደትሽ ተማፅኜሻለሁ
ከልጅሽ አስታርቂኝ ድንግል ብዬሻለሁ

አዝ

ከፍቅርሽ አትለይኝ ደግሞም ከሃይማኖት
ሕጉንም ጠብቄ እንድኖር በሥርዓት
ከለላዬ ሁኝልኝ ጠብቂኝ ከጠላት
ከዚያ ከዲያቢሎስ ከኃጢአት አባት

91. ማርያም ድንግል

ማርያም ማርያም ድንግል ማርያም/2/
ርኅርኅተ ኅሊና/4/ ማርያም/2/

92. የወርቅ መሠላል ነሽ

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ
መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ
ሰውና አምላክን ያገናኘሽ

አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ/2/
አሸልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጤዛ
ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ መሰላል
ምሳሌሽን አየ ማርያም ድንግል

አዝ፣

መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ/2/
እንዳየ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ
ተስፋ አድርጌ ሲኖር የሰላሙን ዘመን
ይኸው ተፈጸመ በአንቺ በእናታችን

አዝ፣....

በአንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም/2/
በአንቺ ተፈጸመ የያዕቆብ ሕልም
ሰውና መላእክት ተለያይተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድነት ዘመሩ

አዝ፣....

93. ማርያም ፈደል ናት

ማርያም ፊደል ናት የሁሉም መማሪያ/2/
በንጽሕና በንጽሕና ተጽፋለችና/4/

94. ሐመልማላዊት ዕፅ

ሙሴ ዘርእየ/2/ በደብረ ሲና/2/
ሐመልማላዊት ዕፅ ሐመልማላዊት/2/

ትርጉም፦ የለመለመች ዕፅ ናት የለመለመች ሙሴ ያያት በደብረሲና የለመለመች ዕፅ ናት የለመለመች

95. ጽላት

ጽላት ዘሙሴ ጽላት/2/ ሕግ ወሥርዓት/2/
ሙሴ ከፈጣሪ የተቀበላት
አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፈባት
ጽላት ዘሙሴ ጽላት

96. ድንግል ሆይ ሰላንቺ

ድንግል ሆይ ስላንቺ ነውና መሐሪ

አማልጂኝ ከአንዱ ልጅሽ ከፈጣሪ
ስሙን እንዳልጠራ አንደበትም የለኝ
ፊቱንም እንዳላይ ሥራዬ አሳፈረኝ
ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ
ትዕዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ
አዝ፣
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሳሪ
አማልደኝ ከጌታዬ ከፈጣሪ
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ
እለምነዋለሁ ከአሁኑ ይቅርታ
አዝ፣
ጻድቃን ሰማዕታት እናንተ ሁላችሁ
አማልዱኝ ከጌታዬ ከአምላካችሁ
አዝ፣

97. ይዌድሰዋ

ይዌድስዋ መላእክት/2/ለማርያም /2/
በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ } 2
በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ
ትርጉም፦በመጋረጃ ውስጥ መላእክት
ማርያምን ያመሰግኗታል ሰላምታ
ይገባሻል ማርያም አዲስቷ እንቦሳ ይሏታል።

98. እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም እለምንሻሁ
በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለሁ
እመቤቴ ስሚኝ እለምንሻለሁ/2/
ኃዘኔን ጭንቀቴን ለማን እነግራለሁ
ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለሁ
እመቤቴ ስሚኝ ተማፅኜሻለሁ/2/
ኃዘኑም በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ
እንደምን ልቻለው እኔ ደካማ ነኝ
የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሺልኝ/2/
በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ
እመ አምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጐኔ
ምንም አጋር የለኝ ከአንቺ በቀር ለኔ/2/

99. የብርሃን መውጫ

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል
የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል/2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር/2/
የዳዊት መሰንቆ የጌዴዎን ጸምር
አፍርታልናለች ያለ ወንድ ዘር/2/
እስኪ እናመስግናት እንዲህ በማለት
ቅድስት እናታችን ስብሕት ወቡርክት
አንቀፀ ብርሃን ምዕራገ ሕይወት
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት
በደኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት/2/

100. ሰአሊለነ ቅድስት

ሰአሊለነ ቅድስት እንልሻለን/2/
እንደ ኤፍሬም እንደአባታችን } 2
ለምኝልን እመቤታችን

ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከዘላለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው
በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው
አዝ
ስምሽም ሥልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃልኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ } 2
አዝ
ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትዝል ሲከብዳት ኃጢአት
ጨልሞብን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን } 2
አዝ
የልባችን ጎዘን እጅጉን ከብዶናል
ኃጢአታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል
አንደ ኤልሳቤጥ አንደዘመድሽ
ደስ አሰኝን ይሰማ ድምፅሽ } 2

አዝ

101. ኢያቄም ወሐና

ኢያቄም ወሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት
የሰጡሽ መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍጹም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሺ
አ/4/ እመ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሺ/2/

102. አንቀፀ ብርሃን

አንቀፀ ብርሃን ድንግል ማርያም/2/
ሰማያዊ ዙፋን የመድኃኔዓለም
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ኧረ እንደምን ቻልሽው መለኮትን
የእሳት መጋረጃ ወዴት ተጋረደ
ልዑል በጥበቡ ከአንቺ ተዋሐደ
ሰማያዊ ንጉሥ የከተመብሽ
የመለኮት ዙፋን ድንግል አንቺ ነሽ
ሚካኤል ገብርኤል ሰግደው ዘመሩልሽ
ሩፋኤል ራጉኤል ሰግደው ዘመሩልሽ

103. ማኅደረ መለኮት

ማኅደረ መለኮት /2/
ማርያም እመብዙኃን/4/
<u>ትርጉም</u>–የመለኮት ማደሪያ የሆንሽ
እመቤታችን ማርያም የብዙኃን እናት ነሽ

104. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ

እመአምላክ ሙሽራ ነሽ } 2
ለቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ እኸ/2/
አሥራሁለት ዓመት ቤተመቅደስ የኖርሽ
የመመረጥ ጸጋ ከጌታ ያገኘሽ
በአብሣሪው መልአክ እጹብ ድንቅ ዜና
ከሰማይ መጣልሽ አቋርጦ ደመና
በስድስተኛው ወር ተልኮ ገብርኤል
ቤተመቅደስ ገባ ሊያበሥራት ለድንግል
በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ ያለሽ
የክርስቶስ እናት በጣም ደስ ይበልሽ
መላእክት በሰማይ ያመሰግኑሻል
ክብር ለአምላክ እናት ይድረሳት ይሉሻል
በማኅፀንሽ ቢያድር የሠራዊት ጌታ
ለመሆን ተመረጥሽ የአምላክ ቅዱስ ቦታ
የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ
ሰላም ላንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነሥቶ
ከፍጡራን ሁሉ አንቺ ትበልጫለሽ
ገብርኤል ተልኮ ደስታን አበሰረሽ
ምንኛ ድንቅ ነው ድንግል የአንቺ
ብሥራት
ጌታን ትወልጃለሽ የሚል ቃልን መስማት
ይሁንልኝ ብለሽ ቃሉን የተቀበልሽ
ድንግል ሆይ እናቴ እጅግ ልዩ እኮነሽ

105. አትለይን

አትለይን /2/ ድንግል ሆይ ድረሽልን/2/
ከዲያብሎስ እጅ አንቺ አድኝን } 2
ምሕረት ከልጅሽ ለምኝልን

106. ንጽሕተ ንጹሐን

ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና ከመታቦት ዘዶር ዘሲና
ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግልና ነበረት
ሲሳያ ኀብስተ መና ውስቴሃኒ ስቴ ጽሙና/2/
<u>ትርጉም</u>– ከንጹሐን ንጹሕ ሆና በሲና እንደ ነበረችው
ታቦት በድንግልና በቤተመቅደስ ውስጥ ኖረች ምግቧ
ኀብስተ መና መጠጧም የፀጥታ መጠጥ ነበር::

107. ኢያቄም ወለዳ

ኢያቄም ወለዳ ኢያቄም/2/
ዳዊት ዘመዳ ኢያቄም ወለዳ/4/
<u>ትርጉም</u>–የኢያቄም ልጅ የዳዊት ዘመድ ናት

108. ምሥራቀ ምሥራቃት

ምሥራቀ ምሥራቃት ሙውዕዐ ፀሐይ/2/
እግዝእትየ ዘመና ሙዳይ/2/
ዘመና ሙዳይ ማርያም ዘመና ሙዳይ /4/
ትርጉም የጎብስት ክርስቶስ መገኛ የወርቅ መሶብ ከፀሐይ መውጫዎች ሁሉ የምትበልጥ የፀሐይ መውጫ /ምሥራቅ/ አንቺ ነሽ::

109. በመኑ
በመኑ በአምሳለ መኑ አስተማስለኪ/2/
እመቤቴ የኔ አማላጅ አዛኝቷ ኦ ድንግል } 2
ምልዕተ ውዳሴ
ትርጉም:- ማን በተመሰለው ምሳሌ እመስልሻለሁ እመቤቴ የኔ አማላጅ አዛኝቷ ምስጋናን የተመላሽ ነሽ::

110. ተወልዳለችና
ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ
መድኃኒት/2/
እናመስግናት እናወድሳት እንውደዳት }
እናመስግናት እናወድሳት እርሷ ናት እና } 2
የአዳም ሕይወት

<u>111 ተፈፀመ ሐና በወለትኪ</u>
/ዲ/ን መገርሳ - ቁ.2/
ተፈፀመ ሐና በወለትኪ /2/
ተስፋ ቅዱሳን አበውኪ
ተስፋ ቅዱሳን አበው } 2/
ተፈፀመ ሐና በልጅሽ /2/
የቅዱሳን ተስፋ ያባቶችሽ /4/ □ሽ
የሚዘመርበት ወቅት፡ ግንቦት 1

112፤ በምን በምን እንመስላት
በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን
ምሳሌ የላትም/፪፤/ ክብሯን የሚመጥን/፪፤/
የሙሴ ፅላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት <u>የሩህሩኃን ርግብ</u>/፪፤/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌድዮን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር
ሆና የተገኘች <u>የአምላክ ማህደር</u>/፪፤/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግስት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ <u>ዓለም ጣጣ</u>/፪፤/
ከማር ይጣፈጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለሙ ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን <u>ይድረስሽ ምስጋና</u>/፪፤ /
አዝ--------

113፤ እመቤቴ ጥላ ከለላዬ
እመቤቴ ጥላ ከለላዬ እረዳቴ የገነት ሙሽራ/፪/
የገነት ሙሽራ/፫/ ማርያም የልዑል ማደሪያ/፪/

114. እመቤታችን ማርያም
እመቤታችን ማርያም ማጎበራችንን } 2
ጠብቂልን በምልጃሽ
ከመናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን }
ሰውረሽ እንድትጠብቂን በምልጃሽ } 2

115. ለእናታችን ቅድስት
ለእናታችን ቅድስት የዓለም ርኅርኅት/2/
እንስገድላት/2/ እንስገድ/2/ በእውነት } 2
ለአምላክ እናት/2/

116. እመቤታችን
እመቤታችን ለአንቺ እናቀርባለን ምስጋና } 2
አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም
መድኃኒት ሆኗልና
ምእመናን ስለአወቁ ደግነትሽን በሙሉ }
ወደ አንቺ ሁል ጊዜ ይማልዳሉ } 2
ከፈጣሪሽ አማልጂን እያሉ/2/

117. ማርያም እመቤቴ

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት
ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት
ከሴቶቹ ሁሉ አንቺ ነሽ የተባረክሽ
የነፃሽ በእውነት
ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔዓለምን
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ድንግል እናታችን ለዚህ የተመረጥሽ
ለምኝልን ለኛ ምሕረትን ከልጅሽ /2/
አዝ
የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት
የሰማዕታት አክሊል የጻድቃን እናት
የእኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ
ወልድን በመውለድሽ ኃዘናችን ጠፋ /2/
አዝ
ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ
መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ
እኛም የአዳም ልጆች ከመሬት ሆነን
ሰአሊለነ ቅድስት እንልሻለን /2/

118. ማርያም ኃዘነ ልቦና

ማርያም ኃዘነ ልቡና ታቀልል/2/
ኃዘነ ልቦና /4/ ታቀልል /2/
ማርያም የልብን ኃዘን ታቀላለች/2/
የልብን ኃዘን /4/ ታቀላለች/2/

119. የሲና ሐመልማል

የሲና ሐመልማል የሙሴ ጽላት/2/
የሲሎንዲስ ጥበብ ዕፀ መድኃኒት/2/
አሁን በምን በምን እንመስልሻለን
ዕፁብ ድንቅ እያልን እናወድስሻለን
አዝ
ያረጁ ፍጥረታት የታደሱብሽ /2/
የሕይወት መሰላል ማርያም አንቺ ነሽ/2
አዝ
የነቢያት ትንቢት የልባችን ተስፋ/2/
በአንቺ መመኪያነት ማኅበራችን ይስፋ/2/
አዝ

120. እመቤታችን ለአንቺ
እመቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል/2/ 2
ከሴቶች ሁሉ/3/ ተመርጠሻል
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል
ተበሰረላት/3/ የመመረጥ ክብር
አዝ
እያረጓጓት የሰማይ መላእክት/2/
ቤተመቅደስ ኖረች/3/ አሥራ ሁለት ዓመት
አዝ
መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት አውቆ/2/
ሰገዳላት/3/ ዘካርያስ ታጥቆ

121. መሠረተ ሕይወት

መሠረተ ሕይወት ማርያም በረድኤት ነይ/2/
ምሕረት ቸርነተን <u>ይዘሽ ከሰማይ</u>/2/
ምሕረት ቸርነተን ይዘሽ ከሰማይ 2
ማርያም ድንግል በረድኤት ነይ

122. ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን

ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ማርያም ውድስት የሕይወት ብርሃን
ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ድንግል የአብርሃም ድንኳን
ሰላም ሰላም ሐረገ ወይን
ያዕቆብ ያየሽ መሰላል
የሰሎሞን ክብር አክሊል
አዝ
ጽላተ ሙሴ የኦሪት
የአሮን በትር መድኃኒት
የዋህ ርግብ የኢያቄም
የነቢያት ተስፋ የአዳም
አዝ
እሳተ መለኮትን የያዝሽ
ምሉዕ አምላክን የወሰንሽ
ቤተመቅደስ የልዑል
ሰላም ለኪ እም ወድንግል

123 የጠሩሽ /ተምሮ ማስተማር ስ/ት/ቤት - ቁ.1/

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ
የበላዔ ሰብእ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት /2/

በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ጽድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል /2/
አዝ . . .
የእሳት ባህርን በአንቺ ተሻግረዋል
የሰይጣንን ጸር በአንቺ ድል ነስተዋል
ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል /2/
አዝ . . .
ነፍሳቸውም ጽድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም በአንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይኝ ስላለች /2/
አዝ . . .
እኔ በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አሳስቢ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ /2/
አዝ . . .
እኛ በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢ እንላለን
በአማላጅነትሽ እንድናለን /2/
አዝ . . .
ምእመናንም በአንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢ ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ /2/
አዝ . . .

124. አንቺ የወይን ሐረግ /መሪ. ዮሐንስ ስመኝ - ቁ.1/

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ
የበዛ/2/
ምግብ ሆኖ /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለኛ
ቤዛ/2/ □ሽ

ባንቺ ስማይነት የወጣው ፀሐይ/2/
ብርሃን ነው /2/ ለፃድቃን ስሙም አዶናይ/2/ □ሽ
አዝ...
ፊደል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ/2/
ለመላእክት/2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ/2/ □ሽ
አዝ...
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኩክብ መገኛ/2/
በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለኛ /2/ □ሽ
አዝ...

125. ሰላም ለኪ ለኖኅ ሐመሩ /ዲ/ን እንግዳወርቅ- ቁ.1/

ሰላም ለኪ ለኖኅ ሐመሩ
ሰላም ለኪ ለአሮን በትሩ
ሰላም ለኪ ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ
ሰላም ለኪ ለጌድዮን ፀምሩ
ሰላም ለኪ ለሰሎሞንም መንበረ ክብሩ
ሰላም ለኪ ለፍሬ ስብሐት መያዙ /2/

እመ እግዚአብሔር ፀባኦት ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ ሠረገላሁ ለአሚናዳብ
ሰላም ለኪ መና ያለብሽ ንጹሕ መሶብ
ሰላም ለኪ ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ
ሰላም ለኪ የይስሐቅ መዓዛ

እንዘ ንሴፈው ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ
ንሰግድ ለኪ

ሰላም ለኪ ኀብስተ መና ዘእስራኤል
ሰላም ለኪ የሰማዕታት ንጹሕ አክሊል
ሰላም ለኪ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና
ሰላም ለኪ የኤልያስ መና

እንዘ ንሴፈው ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ
ንሰግድ ለኪ

126. ወዳጄ ሆይ

/ዓምደ ሃይማኖት ስ/ት/ቤት - ቁ.2/

ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጽሕት አዳራሽ

ሕዝቅኤል ያየሽ የምስራቋ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር
የልዑል ማደሪያ አማናዊት መቅደስ
ስለንጽሕናሽ ምስጋናን እናድርስ

አዝ . . .
ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል
ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለዘርአ ብዕሲ በኅቱም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
አዝ . . .
ምስራቀ ምስራቃት ድንግል ሆይ
አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምትመስይ ፀሐይን
የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ
ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሸሺ
አዝ . . .

127.<u>እናታችን ጽዮን</u>

/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/

እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና
መጠጊያ ማረፊያ ጥላችን ነሽና

ከገነት ብንወጣ ማረፊያ ሆንሽን
የምሕረት ደመና ውኃ ሰጠሽን
የሕይወት እንጀራን አመጣሽልን
በአስራትም በአደራም ለአንቺ ተሰጠን
አዝ . . .
የኤልሳቤጥ አጽናኝ የጭንቅ ቀን
ደራሽ
የኃጢአታችን ብዛት ዳገት ሳይሆንብሽ
ምሥራችን ደስታን ይዘሽልን መጣሽ
ማርያም ስንልሽ ደረስሽልን ፈጥነሽ
አዝ . . .
ውለታሽ ብዙ ነው ከልብ የማይጠፋ
ስምሽ መጽናኛ ነው አዝኖ ለተከፋ
በእንተ ማርያም ብሎ ለለመነ
የሰማይ የምድሩም ማንም አልጨከነ
አዝ . . .
በትራችን አንቺ ነሽ የምትደግፊን
ባሕረ እሳትን የምታሳልፊን
ጽርሐ ሥላሴ ነሽ ማኅደረ መለኮት
ሁልጊዜ አንጠግብሽም እንላለን ብጽዕት
አዝ . . .

128.<u>ሰአሊ ለነ ቅድስት</u>

ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን /2/
እንደ ኤፍሬም እንደአባታችን
ለምኝልን እመቤታችን /2/

ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከዘለዓለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው
በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው
አዝ . . .
ስምሽም ስልጡን ነው
በእግዚአብሔር መንበር
ቃል ኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ
አዝ . . .
ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትዝል ሲከብዳት ኃጢአት
ጨልሞብን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን
አዝ . . .
የልባችን ሐዘን እጅጉን ከብዶናል
ኃጢአታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደዘመድሽ
ደስ አሰኝን ይሰማ ድምጽሽ
አዝ . . .

129. ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳንኪ ኮነ/፪/ ኪዳነ ምህረት/፬/
ለኃጥአን ተስፋነ ኪዳነኪ ኮነ/፬/

ትርጉም፦ ቃል ኪዳንሽ የምሕረት ቃል ኪዳን ሆነ ለኃጥአን ተስፋቸው ሆነ

130. አ ማርያም

አ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወነአብየኪ/ ፪/
እስመ ወለድኪ ለነ መብልዓ ጽድቅ ዘበአማን
ወስቴ ህይወት ዘበአማን/፪/

ትርጉም፦ ማርያም ሆይ ሥለዚህ እንወድሻለን
ከፍ ከፍም እናድርግሻለን

እውነተኛውን የእውነት መብል
እውነተኛውን የሕይወት መጠጥ
ወልደ ሸልናልና

131.፱ **አዕይንታ ዘርግብ**

እዕይንታ <u>ዘርግብ</u>/፪/ እያቄም ወለዳ/፪
ኢያቄም ወለዳ/፫/ ዘርግብ እያቄም ወለዳ <u>እኸ</u>/፫/
ትርጉም፡- አይኗቿ የርግብ ናቸው እያቄም አባታ ነው

132. **መዓዛ አፈዋት**

መዓዛ አፈዋት <u>ማርያም</u> /፪/ ፅጌ መንግስት ቡሩክት/፪/
ፅጌ/፪/ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሃ ወአፅብሃ/፪/
ትርጉም፡- በጎ መዓዛ ያለሽ ሽቱ /ቅመም/ የተባረክሽ የመንግስት /የክብር/ አበባ ማርያም የሰሎሞን የዳዊት የአብርሃና የአጽብሃ ክብራቸው ነሽ።

133.<u>ለድንግል ገብርኤል አብሠራ</u>

ለድንግል <u>ገብርኤል አብሠራ</u> /2/
ሚካኤል/2/ <u>በክነፍ ያራ</u> /2/
መንጦላዕተ ደመና ሠወራ /2/
<u>ትርጉም</u>፡- ድንግልን ገብርኤል አበሠራት ሚካኤል በክንፉ ተሸከማት የደመና መጋረጃ ሰወራት/ጋረዳት/

የደብረ ታቦር መዝሙራት

134.፱ **አማን በአማን**

አማን በአማን /፬/
ተሰብሃ በደብረ ታቦር /፬/
ትርጉም፡

135. **የታቦር ተራራ**

የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይብልሽ /፪/
እግዚአብሔር መለኮቱን ስለገለጸብሽ /፬/

136. **በስመ ዚአከ**

በስመ ዚአከ ይትፌስሁ ዮም/፪/
ታቦር ወአርሞንኤም /፬/

ትርጉም፡ ታቦርና አርሞንኤም በስሙ ዛሬ ደስ ይበላችሁ።

በእንተ መስቀሉ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

137. መርሕ ለፍኖት

ሃሌ ሉያ መርሕ ለፍኖት ሞገሶሙ
ለጻድቃን ሞገስ/2/
ዝንቱ መስቀል ለአዳም ዘአግብአ ውስተ ገነት/2/
ሃሌ ሉያ መሪ ነው በመንገድ ሞገሳቸው
ለጻድቃን ሞገስ/2/
ይኸ መስቀል ነው አዳምን የመለሰው ወደ ገነት/2/

138. መስቀል ብርሃን

መስቀል ብርሃን ኩሉ ዓለም መሠረተ
ቤተክርስቲያን/2/
ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም መስቀል
መድኀን ለእለ ነአምን/2/
መስቀል ብርሃን ነው ለመላው ዓለም
መሠረት ነው ለቤተክርስቲያን/2/
ሰላምን ሰጪ ነው መድኃኔዓለም መስቀል
አዳኝ ነው ለኛ ለምናምን/2/

139. መስቀልከ

መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ/2/
ይኩነነ ቤዛ /4/ መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ/2/

140. ይትቀደስ ስምከ

ይትቀደስ ስምከ በኃይለ መስቀልከ በዕፀ
መስቀልከ ክቡር ዘአእበይኮ ለስምከ/2/
ስብሐት ለከ ለባሕቲትከ ልዑል/4/

141. በመስቀሉ ወበቃሉ

በመስቀሉ ወበቃሉ/2/
አዕበዮሙ ለአበዊነ/4/

142. በወንጌሉ ያመናችሁ

በወንጌሉ ያመናችሁ/2/
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ/2/

143. ኃይልነ ወጸወንነ
ኃይልነ ወጸወንነ ወሞገስ መሞገስነ/2/
ዝንቱ ውእቱ መስቀል/2/

144. ጥልን በመስቀሉ ገደለ
ጥልን በመስቀሉ ገደለ/2/
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሰላምን አደለ/4/

145. መስቀል ኃይልነ
መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንእነ መስቀል ቤዛነ/2/
መድኃኒትነ ለእለ አመነ/4/

146. ጎበ ቀራንዮ
ጎበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት/2/
ቀራንዮ/2/ ጎበ ቀራንዮ/2/
የመስቀሉ ቃል ለእኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው/4/
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው/2/
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ/4/
እንመነው አንካደው ፈጣሪያችን ቸር ነው/2/
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት/4/
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት /4/
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት/2/
ጎበ ጥበባት ጎበ ልሳናት/4/
ዮሐንስ/2/ ወንጌለ ስብከት/2/

147. በመስቀሉ ቤዘወነ
በመስቀሉ ቤዘወነ ወበደሙ ተሰሃለነ/2/
አምላከ ምሕረት ውእቱ መድኃኒነ
አምላከ ምሕረት ውእቱ
በመስቀሉ ቤዛ ሆነን ሞትን ሽሮ ከሞት አዳነን/2/
የምሕረት ጌታ ነውና ይቅር አለን } 2
የምሕረት ጌታ ነውና

148. እሌኒ ንግሥት
እሌኒ ንግሥት ሐሠሥት መስቀሉ/2/
ዕንባቆም ነቢይ ዘአንከረ ክብሩ/2/

149. ብርሃን ወጣ
ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንጸባርቅ
የአምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ እርቅ
ደስ ይበለን በመስቀሉ ብርሃን
እልል እንበል በአንድነት ሆነን
ተነሳልን መድኃኒታችን

ከፊት ለፊት በመሳሉ የመስቀሉ ነገር
የሚወደው ሐዋርያ የወንጌል መምህር
ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ
ሲያዝን ኖረ በምድራዊ ሕይወቱ
ቢያሰቅቀው ሞቱ ግርፋቱ
አዝ
ሞኝነት ነው ለሚጠፉት መሰናከያቸው
በዓለም ጥበብ ለሚኖሩት እውነት ተስኗቸው
ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖረው
የመዳን ቀን እውነተኛ ዓርማ ነው
ከገሀነም እሳት የሚያድን ነው
አዝ
እስከመስቀል ላልተለየው ቅዱስ ሐዋርያ
ለዮሐንስ የወንጌል ሰው የፍቅር ባለሞያ
ምስጋናችን ከምድር ይድረሰው
እንድናለን በሰጠው ምሳሌው
ሰዎች ሁሉ እንከተለው

150. ወሪዶ እምመስቀሉ
ወሪዶ እምመስቀሉ/2/

እምመስቀሉ አብርሃ ለኩሉ
እምመስቀሉ ለኩሉ አብርህ } 2

151 ዮምሰ ለእሊአየ

ዮምሰ ለእሊአየ/2/
አበርህ በመስቀልዬ/2/

በእንተ ቅዱሳን መላእክት

152. ውእቱ ሊቆሙ

ውእቱ ሊቆሙ ለመላእክት ወመልአኮሙ
ስሙ ሚካኤል
ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ
ሊቀመላእክት/2/

ትርጉም፦ የመላእክት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ልብሱ የመብረቅ ዓይኑም የርግብ ነው

153. ልዑል ውእቱ

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/4/
ሚካኤል/2/ ልዑለ መንበር/2/

ትርጉም፦ ከፍ ከፍ ያለነው መቀመጫውም ከፍ ከፍ ያለነው ሚካኤል መቀመጫው ከፍ ከፍ ያለነው

154. ሚካኤል ሊቅ

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ/2/
ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ/4/ ሚካኤል
ሐመልማለ ወርቅ/2/

ትርጉም፦አለቃ የሆነው ሚካኤል ልብሱመብረቅ ነው ዓይኖቹም የርግብ ዓይን ይመስላሉ ሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው

155 ሚካኤል አማልደን

ሚካኤል አማልደን ከአምላካችን/2/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን/4/

156. ቀዋምያን ለነፍሳት

ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት } 2
ዑራኤል ወሩፋኤል
ይትፌነው ለሳሕል/2/እም ኀበ ልዑል
ለነፍሳት የቆሙ እነዚህ መላእክት } 2
ዑራኤልና ሩፋኤል

ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ/2/ ይላካሉ
ከልዑል/2/

157. አምላከ እሥራኤል

አምላከ እሥራኤል ታማኝ ጌታችን
ለእሥራኤል ለሙሴ የሆንከው መድኀን
ፈርያን ቢጸና በትዕቢት ቢገን
ለእሥራኤል አርበኛ መረጥከው ሙሴን
አማላጅ ነው ሚካኤል/2/ የአምላክ ባለሟል } 2
ለነሙሴ ለሕዝበ እስራኤል
ፈርያን እንደገና ልቡ ተጸጽቶ
ቢከተላቸውም ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
አዝ፣....
ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን
እጆቹን ዘረጋ ከፈለው ባሕሩን
እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ
በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ
አዝ፣....

158. መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀመላእክት ዑራኤል/2/
ሰአል ወጸልይ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም

ትርጉም፦የሰላም መልአክ ቅዱስ ዑራኤል ስለ እኛ ለምንልን ጸሎታችንንም በመድኃኔዓለም ፊት አሳርግልን

159. እም እቶነ እሳት
/ሰ/ት/ቤት/ማ.መ - ቁ.1/

እም እቶነ እሳት /2/ ዘይነድድ
አንገፈነ በሰፊሐ እድ ሊቀ መላእክት
/2/ አዝ
ታላቅ መመኪያ ነህ
ለሚያምኑብህ ሁሉ
ናዛዜ ኀዙናን /2/ ገብርኤል
ለልዑል መልአከ ኃይሉ
የነበልባል ኃይሉ ሞገዱ ሲበዛ
ለሠለስቱ ደቂቅ የሆንካቸው ቤዛ
አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
ፈጥነህ የምትደርስ በዕለተ ጻሕቅ

ምስጉን ነህ አንተ ከፍ ያልክ በጽድቅ
አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
ዜናዊ ፍስሐ ለሰው ልጅ ድህነት
የሰላም መልአክ ነህ ሊቀ መላእክት
አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
በአማላጅነትህ እንኮራለን
እኛ ክርስቲያኖች ደቂቀ ጽዮን
አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)

የግእዙ ትርጉም፡- ከሚነደው የእሳት ነበልባል የመላእክት አለቃ እጆቹን ዘርግቶ አተረፈን።
በዕለተ ጻሕቅ፡- በጭንቅ ቀን

<u>160 ከመ ትባርከነ</u>

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/
ተዋነይ በጽድቅ/4/ ገብርኤል ሐመልማለ ወርቅ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- በክቡር መስቀልህ ትባርከን ዘንድ ገብርኤል ሆይ በእውነት በረድኤት ተመላለስ።

161. ፱ ገብርኤል ግሩም

ገብርኤል ግሩም በመንፈስ ቅዱስ ህቱም/፪/
ነዓ/፬/ ማዕከሌነ ቁም በበዓልከ ባርከነ ዮም

ትርጉም፡- በመንፈስ ቅዱስ የታተምህ ኃያል ገብርኤል ሆይ በበአልህ ቀን ትባርከን ዘንድ ና በመካለኞን ቁም

<u>162. ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ</u>
/ሊቀ ጉባዔ ታረቀኝ - ቁ.1/

ሚካኤል <u>ሐመልማለ ወርቅ</u> /2/ ልብሱ ዘመብረቅ
ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ
የወርቅ ልምላሜ
የወርቅ ልምላሜ ና ና ና
ስለምንህ ቆሜ
አዝ . . . ሚካኤል

ገብርኤል <u>ሊቀመላእክት</u> /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት
በሠለስቱ ደቂቅ ናቡከደነፆር ተቆጣ
እሳቱ ነደደ ነበልባሉ ወጣ
ግን ኃያል ገብርኤል
ሊያድናቸው መጣ
አዝ . . . ገብርኤል
ሠለስቱ ደቂቅ ይባርክዎ
ለእግዚአብሔር
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ብለው
ምስጋና አቀረቡ ከእሳቱ ላይ ሆነው
አዝ . . . ገብርኤል

ራጉኤል <u>ሊቀመላእክት</u> /2/
እምህበ ላዕል ወረደ /2/
መጋቤ ብርሃናት አንሶሳዊ ፋና
ራጉኤል ና ና
ና ና ና አማላጅ ነህና
አዝ . . . ራጉኤል

ኡራኤል <u>ሊቀመላእክት</u> /2/
ለዕዝራ ያጠጣህ ጽዋአ ሕይወት
በዓለም ፈተና በስቃይ ኩነኔ
ስባዝን ስጨነቅ ስጠበብ ወይ እኔ
ኡራኤል የእኔ ኃይል ቁምልኝ ከጎኔ
አዝ . . . ኡራኤል

በእንተ ቅዱሳን

163.ቅዱሳን መስክሩ

ተአምሩን ያያችሁ ቅዱሳን መስክሩ
ፍቅሩን ቸርነቱን ለዓለም ንገሩ/2/
በየዋሕ ልቡና ንጹሕ መሰዋትን
አቤል ግለጥልን ለጽድቅ መሞትን
ኖኅም ተናገረው ለአንተ የታየህን
ዛሬን ብቻ ትተህ ነገን ማሰብህን
አዝ
ተናገር አብርሃም የአምላክን ሥራ
እንዴት እንደነበር ያኔ ስትጠራ
ልጅህን ያሠጠህ ፍቅሩን ግለጥልን
በእምነት መታዘዝን ለእኛም አስተምረን
አዝ
ግለጥልን ዮሴፍ እንዴት እንደነበር
ፍትዎትን ድል ነሥቶ ለሃይማኖት ማደር
ከራስ ተድላ ይልቅ ለወገን መሞትን
አስተምረን ሙሴ ፍቅርና ጽናትን
አዝ
ለጠላት መጸለይ በማድረግ ይቅርታ
አሳይ እስጢፋኖስ የፍቅርን እውነታ
በፈተና ብዛት እንዳናመነታ
ቂርቆስ ጽኑ በለን ልባችን ይበርታ
አዝ
164. መሠረተ ዜማ
መሠረተ ዜማ ወጠነ/2/ ያሬድ ካህን/2/

ያሬድ /3/ **ያሬድ ካህን ጥዑመ ልሳን**

<u>ትርጉም</u>፦የዜማ መሠረትን ያሬድ ጀመረ
ካህኑ ያሬድ አንደበቱ ያማረ ነው

165. ብርሃናተ ዓለም

ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ
ጻድቁ አባታችን/2/ **ገብረመንፈስ ቅዱስ**/2/
የመረጣችሁ ፈጣሪያችን አምላካችን
እንድናገኝ ሰላምን አማልዱን እኛን
ከፈጣሪያችን/2/

166. ደም ወማይ

ደም ወማይ ወሀሊብ እምነ ክሳዱ
ፈልፈለ/2/ /2/
ሶበ ተከለለ/2/ **ተከለለ ቅዱስ ጊዮርጊስ** /2/
<u>ትርጉም</u>፦ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰይፍ
አንገቱን በተሰየፈ ጊዜ ደም ውኃና ወተት ፈሰሰ

167. ጊዮርጊስ ኃያል

ጊዮርጊስ ኃያል/2/ **መስተጋድል**/2/
ገባሬ ተአምር/2/ **ኮከበ ክብር**/4/
<u>ትርጉም</u>፦ጊዮርጊስ ኦርቦኛ ኃይለኛ ተጋዳይ
ነው አስደናቂ ተአምር የሚሠራ ተጋዳይ ነው

168. ኮከብ ብሩህ

ኮከብ ብሩህ ቅዱስ ማርቆስ ዘሠረቀ እም
እስክንድርያ
ቤተክርስቲያን ዘንሰምያ/2/
ኮኖሙ አበ ለሰብአ ግብፅ ወኢትዮጵያ
በከመ ጳውሎስ ሐዋርያ
<u>ትርጉም</u>፦ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተገኘዉ ብሩህ
ኮከብ የሆነው ቅዱስ ማርቆስ እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ
ለኢትዮጵያና ለግብፅ ሰዎች አባት ሆናቸው

169. በብዙ አህጉር

በብዙ አህጉር የዞርክ የጌታን ወንጌል
ያስተማርክ/2/
የዲቁናን ግብር በክብር የፈፀምክ ብፁዕ ነህ
ብፁዕ ነህ እስጢፋኖስ ብፁዕ ነህ

2

170. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረመንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን
ናቸው/2/
ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው/2/

171. ተክለሃይማኖት

ተክለሃይማኖት የዓለም ብርሃን ናቸው/2/
ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው/2/

172. ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ/2/ **ለገብረመንፈስ ቅዱስ**
ከመጼና ስሒን/2/
አልባሲሁ ዘሜላት/2/ **ዘወረደ ውስተገነት**/2/
<u>ትርጉም</u>፦የገብረመንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው
ከገነት እንደ ወረደ ነጭ ሐር ነው

173. አባ አቡነ

አባ አቡነ/2/ **መምህርነ**
አባተክለሃይማኖት/2/
እምአእላፍ ጎሩይ/2/ **አባ**/6/ **አቡነ**
ተክለሃይማኖት/2/
<u>ትርጉም</u>፦ መምህራችን አባ ተክለሃይማኖት ከብዙዎቹ
መካከል የተመረጥክ ነህ

174. ጻድቃንሰ ኢሞቱ

ጻድቃንሰ ኢሞቱ ጎበ እግዚአሙ ነገዱ/2/
በመንግሥተ ሰማይ/4/ **ይሁቦሙ ዘፈቀዱ**/2/
<u>ትርጉም</u>፦ ጻድቃን አልሞቱም ነገር ግን ወደ ጌታቸው
ሄዱ እርሱም በሰማያዊ ቤቱ የወደዱትን ሰጣቸው

175. ጻድቃን ቡሩካን

ጻድቃን ቡሩካን ዓለምን ንቃችሁ
የክርስቶስን ፈለግ የተከተላችሁ
በመንግሥተ ሰማይ እጥፍ ነው ዋጋችሁ
ሰአሉ ለነ አሰተምሕሩ ለነ
እስመ በጸሎተ ጻድቃን ትድኅን
ወኢትማስን ሀገር
ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስ ዲያቆን
ወቅዱስ ጊዮርጊስ መክብበ አሚን

ወኢየሉጣ ወቂርቆስ ሕፃን

አዝ.....

ገብረመንፈስ ቅድስ ዘእምአቅሌስያ

ወተክለሃይማኖት ዘኢትዮጰያ

ወማርቆስ አብ ዘእስክንድርያ

አዝ.....

176. ትቄድሶ ደብረ ሊባኖስ

ለተክለሃይማኖት ጻድቅ መጠነ በዝኃ

ሕማሙ/2/

ትቄድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ/4/

እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍለሰተ ሥጋሁ

ወአፅሙ/2/

አዝ.....

እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለዓለት በስሙ/2/

አዝ.....

ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ/2/

አዝ.....

<u>ትርጉም</u>፦ ጻዲቁ ተክለሃይማኖት ብዙ ሕማም የተቀበለባት የሥጋውና የአፅሙ ፍልሰት የተደረገባት በስሙ ከተሰየሙ አድባራት በላይ የሆነች ኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የቀደሳት

ደብረሊባኖስ ተክለሃይማኖትን ታመሰግናለች

177. እንደ አናንያ

እንደ አናንያ እንደ አዛርያ እንደ ሚሳኤል } 2

አጽናን እኛን

አጽናን እኛን/2/ **አጽናን እኛንም**

በእምነታችን/2/

178.<u>ሕፃን ወእሙ</u>

ሕፃን ወእሙ /3/
ክልኤሆሙ ፈፀሙ ገድሎሙ /2/
ሕፃን ንዑስ /3/
ዘኢፈርኃ ትእዛዘ ንጉሥ /2/

<u>ትርጉም</u>፦ ሕፃን እና እናቱ (ቂርቆስ እና ኢየሉጣ) ሁለቱም ገድላቸውን ፈፀሙ። ታናሹ ሕፃን (ቂርቆስ) የንጉሡን ትእዛዝ አልፈራም።

<u>179 ኦ ፍጡነ ረድኤት</u>

/ማ/ሥላሴ - ቁ. 4/

ኦ <u>ፍጡነ ረድኤት</u> /2/

የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ሰማዕት

ሰላም ላንተ ይሁን - ፍጡነ ረድኤት

የልዳው ፀሐይ - ፍጡነ ረድኤት

በጨካኝ ንጉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ

ታማኝ አገልጋይ ነህ - ፍጡነ ረድኤት

ስቃይ ያልበገረህ - ፍጡነ ረድኤት

አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ

ለእምነቱ ተጋዳይ - ፍጡነ ረድኤት

ታማኝ ወታደር - ፍጡነ ረድኤት

ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር

ስቃይ ሲያደርሱብህ - ፍጡነ ረድኤት

በመታገስህ - ፍጡነ ረድኤት

ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ

የፈጣሪውን ስም - ፍጡነ ረድኤት

ስለመሰከረ - ፍጡነ ረድኤት

ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ

የስቃይ መሳሪያ - ፍጡነ ረድኤት

ያላዘናጋህ - ፍጡነ ረድኤት

መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ

ለሰማው ይደንቃል - ፍጡነ ረድኤት

የአንተ ሰማዕትነት - ፍጡነ ረድኤት

ምሳሌ ይሆናል ለሁሉም ፍጥረት

ገድልህ ይናገራል - ፍጡነ ረድኤት

ክብር እንደተሰጠህ - ፍጡነ ረድኤት

ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖት

አዝ . . .

180 <u>ወጽአ አ እምድረ ካራን</u>

ወጽአ እምድረ ካራን ወቦአ ብሔረ ከነዓን /2/
ተአመነ አብርሃም /2/ በእግዚአብሔር። /2/

<u>ትርጉም</u>፦ ከካራን ምድር ወጥቶ ወደ ከነዓን ሀገር ገባ። አብርሃም በእግዚአብሔር ታመነ።

መዝሙረ ንሰሐ

181. ስብሐት ለአብ

ስበሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅድስ

ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም

ምስጋና ከማቅረብ <u>ከቶ አንወሰንም</u>/፪/

ዛሬም ወደ ፊትም ደግሞም ለዘለዓለም

ከዚህ ከማራኪው ካሰጨናቂው ዓለም
የጠራ ይድናል <u>የፈጣሪውን ስም/፪/</u>
በእውነት ያለ ሀሰት ያለ ጥርጥር
ከቶ መድሀኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሮአችን እንዲያምር <u>አንድነታችንም/፪/</u>
ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም
ያልከውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ
ሁለት ሶስት ሆናችሁ <u>በስሜ ካለችሁ/፪/</u>
እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ
አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንህለን
እንድትገኝልን <u>በመካከላችን/፪/</u>
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሆነን

182.. አልተወኝም ጌታ

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል/2/
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነሽ ይለኛል
በበደል ጉራንጉር በኃጢአት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል } 2
አዝ ....
ለስልጣን ለክብር ብዬ ስክደው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ብረሳው
ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም } 2
አዝ .....
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫ መቃብር ላወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ሁሉ ፍጹም ለመራኝ
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ } 2
አዝ ....

183. በረቀቀው ፍቅርህ

በረቀቀው ፍቅርህ አንተ ብትጠራኝ ዛሬ
ይኸው ዳግመኛ መጣሁ በኃጢአት ዓለም
ኖሬ/2/
ከቤትህ እርቄ ብሄድ ለዓለም ተገዛሁ
አንተ ይቅር ትለኝ ዘንድ እንደገና መጣሁ/2/
በቆረስከው ሥጋህ ባፈሰስከው ደምህ
ከዓለም ግዞት አውጥተህ አኑረኝ በቤትህ/2/
ዳግመኛ እንዳልበድልህ በዓለም ተታልዬ
በቅዱሳንህ ምልጃ ጠብቀኝ ጌታዬ/2/
በዓለም የሠራሁትን ያሳዘንኩህን ሁሉ
ይቅር በለኝ አምላኬ ስለ እግዝእትነ
ኩሉ/2/

184. አቤቱ ፈጣሪያችን

አቤቱ ፈጣሪያችን መድኃኒታችን
አምላካችን አባታችን
በአንተ ላይ ነው ዘለዓለም ተስፋችን
ቀንና ሌሊቱን የምታፈራርቅ
አምላክ አንተ ብቻ ሥራህ የሚያስደንቅ
አዝ፣....
መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ
በረቂቅ ሥልጣንህ ሁሉን የምትገዛ
አዝ፣.....
በበደልነው በደል በሠራነው ሥራ
ስለኛ ተቀበልክ ያን ሁሉ መከራ
አዝ፣....
ሰይጣን በተንኰሉ እንዳያጠምደን
በሕይወት ጐዳና ወደአንተ ምራን
አዝ፣....
የዘላለም አምላክ የፍቅር የሰላም
አቤቱ ተመስገን እስከዘለዓለም
አዝ፣....

185. ንሰሐ እንግባ

ንሰሐ እንግባ ኃጢአት መሥራት ይቅር/2/
የአምላክ ባለሟሎች እንሁን በምግባር/2/

186. ወደ ሕይወት መንገድ

ወደ ሕይወት መንገድ ይመራኛል ጌታ
በጨለማው መንገድ እንዳልንገላታ/2/
ፈጣሪ ብቻ ነው ሕይወቴና ክብሬ
ለርሱ ደስ ይለኛል ሳቀርብ ዝማሬ/2/
ጉልበት ሁሉ ላንተ በፍርሃት ይሰግዳል }

ምሕረትን አድለን ፈጣሪ ቸል አትበል/2/
የሕይወትን ውኃ የተጠሙ ሁሉ
ከኃያሉ ጌታ ከአንተ ይረካሉ/2/
በምሕረትህ ማረን አቤቱ ፈጣሪ
ለፍጥረታት ሁሉ ነህና መሐሪ/2/
ሰላምን አድላት ለኢትዮጵያ/2/
እጆቿን ዘርግታ ስትል ሃሌ ሉያ/2/

187. ዓለምን ዞሬ

ዓለምን ዞሬ አየሁት
ሁሉን በተራ ቀመስኩት
ፈጽሞ የለም/2/ ሰላም እንደልጅሽ ቤት
ሀብት ንብረቴን ጨረስኩና
ጉልበቴ ሁሉ ደከመና
ጐስቋላ ሆንኩኝ /2/ ደካማ የሌለው ጤና
ስቃ አሳስቃ ተቀብላ
መልኳን አስውባ ተኳኩላ
ዛሬ ጣለችኝ/2/ ይህች ዓለም አይረባም ብላ
የትናንትና ወዳጆቼ
ዛሬ ሲሆኑኝ ጠላቶቼ
ባክኜ ቀረሁ/2/ በዓለም ላይ ተንከራትቼ
የአባቴ ቤት ሲናፍቀኝ
ፍቅሩ ምሕረቱ ትዝ ሲለኝ
ሁሉንም ትቼ/2/ ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ
ልጁም እንድባል ባይገባኝ
ባርያው እሆን ዘንድ ቢፈቅድልኝ ጐስቋላው
ልጁ ደካማው ልጁ ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ
እናቴ አንቺን ንቄ ትቼ
የአባቴን ቤት እረስቼ
ተሰቃየሁኝ ተንከራተትኩኝ ልደሰት በዓለም
ገብቼ
አባቴ ሲያየኝ ተደሰቶ
ጐረቤቶቹን ሁሉ ጠርቶ
ሠርጉን ደገሰ/2/ የበደልኩትን ረስቶ
አስከ አሁን ድረስ በድያለሁ
ዓለም ደህና ሁኝ አብቅቻለሁ
ወደ አባቴ ቤት/2/ ዳግመኛ ተመልሻለሁ/3/

188.. የሰው ልጅ ሁልጊዜ

የሰው ልጅ ሁልጊዜ በጣም ደስ ቢለው/2/
ደግሞም የጭንቁን ቀን ማሰብ ተገቢ ነው/2/
ምንም ቢደሰቱ ቢበዛ ምኞት/2/
አይቀርም በኋላ መወሰድ በሞት
ችግር ቢፈራረቅ ጎዘን ቢከበን/2
ከክርስቶስ ፍቅር ማንም አይለየን/2/
ሳናውቀው ዲያብሎስ እንዳይነጣጥለን/2/
ነቅተን እንጠብቀው የእምነትን ሰይፍ ይዘን

189. የሰው ልጆች ሁላችን እንማር

የሰው ልጆች ሁላችን እንማር
አስተባብረን ሃይማኖት ከምግባር

የሰው ልጆች ሁላችን እንማር
መልካም ሥራ በመሥራት እንኑር
የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መውረሻ
ሃይማኖት ናትና እውነተኛ ጋሻ
አዝ ....
ለእውነተኛ ሥራ ሁላችን እንበርታ
ጻድቃን ሰማዕታትን አድርገን መከታ
አዝ ....
ፍጻ ዓለምን አልፈን እንድንሄድ ሁላችን
ፀንተን መገኘት ነው በሃይማኖታችን
አዝ.....
እምነታችን ሁሉ ይሁን በፈጣሪ
ይቅር ባይ ነውና ፈጽሞ መሐሪ
አዝ...

190 ፪ ልመናዬን ስማኝ

ልመናዬን ስማኝ ቃሌንም አድምጥ
እውነተኛው አምላክ ሰላምህን ስጥ
ክርስቲያኖች ሁሉ ትዕዛዙን አክብሩ
ምስጋናን አቅርቡ ስገዱ ዘምሩ
የጌታን አመጣጥ ለዓለም ንገሩ
ደቀመዛሙርቱ ወንጌል አስተምሩ

በመልካም የሚሄድ ጽድቅን የሚሠራ
የፈጣሪውን ሥም በከንቱ የማይጠራ
ይጎበኛል በምድር በሠማዩም ሥፍራ
በቀኝ ይቀመጣል ከቅዱሳን ጋር
ስለጠላቶቼ በጽድቅ ምራኝ
በጥል ከበቡኝ ተሰለፉብኝ
መሐሪ ይቅር ባይ መጠጊያ ሁነኝ
አንተ በቸርነት ይቅርታን ስጠኝ

191. አንድ ጊዜ የአግዚአብሔር ሆኛለሁ
አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሆኛለሁ
በፍቅሩ ተስቤ በደሙ ድኛለሁ
ዓለም ተይኝ ንቂ ትቼሻለሁ
ጥበበኛው ሰይጣን በመጣው ቢመጣ
ዳግም ተመልሼ ከእግዚአብሔር
ላልወጣ
ከመስቀሉ ግርጌ አርፌ እኖራለሁ
ዓለም ተይኝ ንቂ ትቼሻለሁ
አዝ፣....
ቢያሙኝ ቢያንቋሽሹኝ ቢሳለቁብኝ
ውርደትም ተንኰልም ቢሸርቡብኝ
ለኔ እንደው ደስታ ነው ኃዘንም የለኝ
ሰይጣን እፈር የክርስቶስ ነኝ
አዝ፣.....
ጓደኞቼም ጠሉኝ ተለውጬባቸው
የጥንቱን ጠባዬን ስለነፈኳቸው
ብቻዬን የሆንኩኝ ቢመስለኝም ለኔ
ጌታ እንደሆን አለልኝ ከጐኔ
አዝ፣.....

192. ወዳንተ እሰግዳለሁ
ወዳንተ እሰግዳለሁ ሳለሁ በሕይወቴ
ላንተም እገዛለሁ እስከ ዕለተ ሞቴ
አንተ ነህና መድኃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ/2/
ሳይመሽብኝ ቀኑ ሳይጨልም ድንገት
በጽድቅህ ጐዳና ልጓዝ ወደፊት
ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት/2/
የነፍስ የሥጋዬ የሕይወቴ ቤዛ
አትበለኝ ችላ በደሌ ቢበዛ
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እሄዳለሁ } 2
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እደርሳለሁ }

<u>መዝሙር በእንተ ቤተ ክርስቲያን</u>

193. <u>የቅዱሳን በዓት</u>
/ማ. ቅዱሳን - ቁ.3/
ልቡና የሚመስጥ መዓዛ እጣኗ
ሕሊናን ይገዛል ዝማሬ ድጓዋ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው }
ቤተ ክርስቲያን ናት አምባ
መጠጊያቸው

አዝ
የመላእክት ዜማ የአዕዋፍ ዝማሬ
የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
አዝ . . .
ይዘምሩባታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ፀናፅል ከበሮው
አዝ . . .
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያገኟት በፍልሚያ
አዝ . . .
የገድላቸው ተዓምር መንበግበጊያ መቅረዝ
የሰማዕታት አክሊል የሥራቸው ደሞዝ
አዝ . . .
መውደቂያዬ ይሁን ከመቃብራቸው
ይፈውሳልና ተረፈ አጽማቸው
አዝ . . .
ከኃጥአን ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በዓት ልትሆነኝ ሀገሬ
አዝ . . .

194፱ የድሆች መጠጊያ
የድሆች መጠጊያ ቤተ-ክርስቲያን /፪/
እነሆ ተደሠች ልጆችሽ መጣን
ሠላም ሠላም <u>የዘለዓለም ቤቴ</u>/፪/
ካንቺ አልለይም እስከ ዕለተ ሞቴ
ሠላም ላንቺ ይሁን ቤተ-ክርስቲያን/፪/
በደሙ ያፀናሽ ኢየሱስ መድህን/፪/
ቤተ-ክርስትያን ሆይ የአማንያን እናት/፪/
ወደ አንቺ ቀርበናል እንድናገኝ ህይወት/፪/
ቅረቡ ምዕመናን በአንድነት ሆናችሁ /፪.
እጆቿን ዘርግታ ልተቀበላቸሁ
ተነስታለችና ቅድስት እናታችሁ
አዝ.....

195 እንኳን ደህና መጣችሁ
እንኳን ደህና መጣቸሁ/፪/
ወደ እኔ ወደ እናታችሁ
እጄን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ
ወላጆቻችሁን እንድታከብሩ
አምላካችን <u>መናገሩ</u>/፪/

እንድትፈፅሙ ትዕዛዙን
እምቢተኞች <u>ባለመሆን/፪/</u>
የፅውቀት ገበያተኞች እንደመሆናችሁ
ምንም ጊዜ <u>ባይኖራችሁ/፪/</u>
ከሰኞ እስከ አርብ እየሠራን
እንጠያየቅ <u>በሰንበት ቀን/፪/</u>
እንደዚህ እኮ የምላችሁ
ቤተክርስቲያን ነኝ <u>እናታችሁ/2/</u>
ስለመጣችሁ እናንተ ልጆቼ
ታዩኛላችሁ <u>ተደስቼ/፪/</u>
አዝ----------

196 ወደ ቤተ እግዚአብሔር
ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ሲሉኝ
እንደ ዳዊት እንደ ንጉሱ ተደስትኩኝ
መላዕክት በሰማይ የሚያመሰግኑህ
አምላካችን ፈቃድህ ይሁን እንዘምርልህ
ሞትን አሸንፎ ለተነሳው ጌታ
ዘምሩለት ተቀኙለት በጧት በማታ
በመስቀል ላይ ሳለ ሲወጋ ጎኑን
ውሀና ደም ባንድ ላይ ሆኖ ፈሰሰልን
በውሀው ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን
መንግሥቱን እንድንወርስ ስላደረገን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የጌታችን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የአምላካችን

መዝሙር በእንተ ዓውደ ዓመት
197፻. ጸሊ ኃበ አምላክ
ጸሊ ኃበ አምላክ/፪/ ራጉኤል መልዐክ/፪/
ዐውደ ዓመት ከመ ይትባረክ/፬/
ትርጉም፦ ዐውደ አመቱ እንዲባረክ ራጉኤል ሆይ ወደ አምላክ ፀልይ
198፻፻ እምሔሶ ለሔሮድስ
እምሔሶ ለሔሮድስ ይብላዕ <u>መሐሳሁ/፬/</u> እም
ያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ/፬/
አቢይ ነቢይ ሰባኬ ጥምቀት/፬/
ትርጉም፦ ሔሮድስ ዋና ነቢይ የሆነውንና የጥምቀት ሰባኪ የዮሐንስ አንገት ከሚያሰቆርጥ መሀላውን ቢበላ ይሻለው ነበር

199፻ ራጉኤል እምሰማያት
ራጉኤል እምሰማይት/፪/
እምሉዐላን ወረደ እምልዐላን/፬/
ትርጉም፦

200. ወአንተኒ ህፃን
ወአንተኒ ህፃን ነቢየ ልዑል/፬/
አርኩ ለመርዓዊ <u>ትሰመይ/፪/</u> ነቢየ ልዑል/፪/
ትርጉም፡ አንተ ህፃን የልዑል ነቢይ የሙሽራው ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ትባላለህ /ትሰኛለህ/

201. የአዋጅ ነጋሪ ቃል
የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሃ አየለ
የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
ዐውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም
ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካለተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመሥርት ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ለመጭው ህብታችን
አዝ ....
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራሄ በኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል
አዝ ....
ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንፃን አደራህን
በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህን
አዝ ....